# ሙያና ሥነ-ምግባር

*በላይነህ አባተ* (abatebelai@yahoo.com)

ሐፍቲግተን ፖስት የተባለ ጋዜጣ እ.ኤ.አ.አቆጣጠር በመስከረም 28 ቀን ሁለት ሺህ ዘጠኝ ዓ.ም. እትሙ ወይዘሮ ዘምዘም ሙስጠፋን እንደ ምሳሌ በመውሰድ የኢትዮጵያን ወላዶች ፍዳ ለማሳየት ሞክሯል። [አንብበውት ካልሆነ ዋቢ-1 በመጫን ይመልከቱ።] እኛ መቼም የራሳችንን ጉድ የምንሰማው በእኛው ጋዜጠኞች አንደበት ሳይሆን በሌሎች በኩል ነው። ጸሐፊዋ እንዲያው እግራቸው ጥሏቸው በደረሱበት ያዩትን አወሱ እጅ በጠቢያ ውስጥ ከዚህም የከፉ አያሌ ግፎች ይፈጸማሉ። ጤና ጣቢያ ወይም ሆስፒታል የሚባለውን ቃል ጭራሽ ሳያውቁ እቤታቸው ተሰቃይተውና ኣቃስተው ይህችን አለም የሚለዩ ወላዶች፣ ህጻናት፣ ጎልማሳና አዛውንት ተቆጥረው አያልቁም። እርግጥ ነው በርሃብ ወለድ በሽታ የሚሰቃይ ልጅ መከላከል በሚቻል ደዌ የሞተችውን እናቱን ጡት እንደጎረሰ ያለፈበት ጊዜ አለ። ይህ ሁሉ የሚሆነው እነዚህ በዚያች አገር የተፈጠሩ መከረኞች በገበሩት ግብር ወይም በነሱ ስም በተለመነ እርጥባን እነ "ስም- አይጠሩ" አለመጠን የበሉት ሆዳቸውን በጎራብጣቸው ቁጥር ቻርተር አውሮፕላን እያዘዙ በአውሮጳ፣ በአሜሪካ፣ በኤስያና በደቡብ አፍሪካ በሚታከሙበት ሰዓት ነው።

ጽሑፉ የአሜሪካንና የኢትዮጵያን የወላድ ሞት መጠን የሰማይና የመሬትን ያህል የሚራራቁ መሆናቸውን ለማሳየትም ሞክሯል። እንደሚታወቀው የህጻናት ሞትና የወላድ ሞት መጠን (infant and maternal mortality rates) እንደ አንድ አገር የእድገት መለኪያ መንገዶች ይቆጠራሉ። የአለም ጤና ድርጅት የጤና ማህደር እንደሚያሳየው የኢትዮጵያ የህጻናት ሞት መጠን 77/1000 ሲሆን የወላዶች ደግሞ 720/100, 000 ነው። በአንጻሩ የዴንማርክ የህጻናትና የወላዶች ሞት መጠን ደግሞ እንደ ቅደም ተከተላቸው 3/1000ና 3/100, 000 ነው። ይህ ማለት የእኛ አገር ወላዶች በሃያ አንደኛው ክፍለ-ዘመን እንኳን 240 እጥፍ ያልቃሉ ማለት ነው። [2]

በዴንማርክ የሚወለዱትና የሚሞቱት ሰዎች ምዝገባ ሽፋን (birth and death registration coverage) 100% አካባቢ ሲሆን እነዚህ ቁጥሮች በኢትዮጵያ በዚሁ ቅደም ተከተል ከ7% እና ከ25% ያነሱ ናቸው።[2] ነገር ግን ከዚህ በፊት በሌላ ጽሑፍ ለመጠቆም እንደሞከርኩት የአለም የጤና ድርጅት ይህንን አሐዝ በመዝገቡ ያስቀምጥ እንጅ ከአፍሪካ መረጃውን የሚያገኘው ከእነዚሁ ከወላዶችና ከህጻናት ጉረሮ እየሞለቀቁ ከሚበሉ ግፍ-የማይፈሩ ባለስልጣኖች ቢሮ ነው። በጣም ዝቅተኛ የሆነውን የልደትና የሞት ምዝገባ ሽፋኑን ልብ ብሎ የተመለከተ ለኢትዮጵያ የተሰጡት የጤና መለኪያ አሐዞች ምን ያህል ታማኝነት የጎደላቸው እንደሆኑ መገመት አይሳነውም። እንደምታውቁት የቤታችንን ጉድ ከአለም የጤና ድርጅት የበለጠ እኛ እናውቃለን። ግልጡን እንነጋገር ከተባለ እምነት የሚጣልበት የመረጃ አያያዝ ስርዓት በአገሪቱ የለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር ሰማንያ ሚሊዮን ደረሰ የሚለው ወሬ ሁሉ ተጨባጭ መረጃ የለውም። እንዲያው ለምሳሌ ያህል የጤናውን ሁኔታ አነሳሁት እንጅ ስለ ሌሎች ሕዝባዊ አገልግሎቶችም ሆነ የኢኮኖሚ እድገት የሚሰጠው መረጃ ሁሉ በየአመቱ ከሚያብለጨልጭ ጠረጴዛ ላይ ክንድን ጣል አድርጎ በድሃ ወዝ የወዛውን ጢም እያሻሹ ፈረንጅ በሰራው ኮቢ የሚፈጠር ወይም በተውሶ ቃል አገላለጥ የሚፈበረክ ነው። እንደ አለመታደል ጦቢያ በምግብና ውሃ አቅርቦት፣ በመብራት፣ በስልክ፣ በኢንተርኔት፣ በመንገድ ትራንስፖርት፣ በትምህርትና በሌሎችም የአገልግሎት ዘርፎች ሁሉ ውራ መሆንዋ የአደባባይ ሚስጢር ነው።

አዎ ከሩጫ በስተቀር በሌሎች አብዛኛው የሕዝብ መመዘኛ ዘርፎች ሁሉ ጭራ ነን። እርግጥ ነው ጦቢያን ድሃ ያደረጋት ዘመን የማይሽረው የመልካም አስተዳደር ድርቅ እንጅ የዝናብ ማነስ ወይም የተፈጥሮ ሐብት እጥረት አይደለም። ለዚህ ደግሞ ብዙ ጊዜ ኮቢ ሳይሆን ጠመንጃ ማንሳት የሚቀናቸው፣ የአስተሳሰብ አልማዛቸው ከጡንቻ የተሰራ፣ ከሰላም ይልቅ ሽብርና ረብሻ የሚወዱ አምባ ገነኖች ተጠያቂ ይደረጋሉ። በኔ እምነት ከነሱም በተጨማሪ "ኮቢን ከወረቀት አገናኝቻለሁ፣ ድን ጾመ-ድጓን ተወጥቻለሁ፣ ዩንቨርሲቲን በጥሻለሁ፣ ዲግሪ ጭኛለሁ፣ ቆብ ደፍቻለሁ፣ ቀስቻለሁ ፣ ጸጽቻለሁ ወይም ደግሞ ለሃጅና ሽህነት በቅቻለሁ" የምንል ሁሉ የሙያ አደራ በላዎችና ተጠያቂዎች ነን። እኛ ጉደኞች በሰላም ጊዜ አለባበሳችንን እያሳመርን፣ጢማችንን እያስረዘምን፣ ዘመናዊ ምሁርን ነን የምንል ታሪክን እያጣቀስን፤ ካህን ነን ባዮችም "የግእዝ ቃላትን እንደ ቋንጣ ጣል ጣል እያድረገን ድስኩር እናበዛለን። አዎ በደግ ቀን ጊዜ እግራችን ቀደም ቀደም፣ ምላሳችን ፈጠን ፈጠን ይላል። ከፊት ለመታየት እንሽቀዳደማለን። እንደ አሁኑ አይነት ጭንቅ ያለና አስተዛዛቢ ቀን ሲመጣ ደግሞ ሁለት መልክ ያለው ጃኬት እንለብስና ቀን ቀን ከተገዳይ ወዳጆች ጋር ውለን ማታ ማታ ደግሞ ከገዳዮች ጋር ውል እንዋዋላለን። አንዳንዶቻችንም ህሊናን በሳሙና ሙልጭ አድርገን እናጥብና "ጊዜውን መሰሎ መኖር" በሚል የስግብግብነት

መርህ ጭልጥ ብለን የደም ጅረት ከሚያወርዱ ባለጊዜዎች ጋር ተሰልፈን የወንጀሉ ተቋዳሽ እንሆናለን። አዎ መቼም ተጠያቂነትን  በጸጋ የሚቀበል ብዙ አይደለም እንጅ እኛ ፊደል ቆጣሪዎች በሚገባ ተጠያቂዎች ነን። ተጠያቂ የምንሆንበት ምክንያትም ሕዝብን የደም እንባ ለሚያስለቅሱት ታማኝ አገልጋይ በመሆናችን አለዚያም እንዲህ አይነቱን ፍዳ ዝም ብለን በመመልከታችን ወይም “አናይም አንሰማም” እያልን ተደብቀን እንደ ቅንቡርስ ስንበላ ኖረን ለመሞት በመወሰናችን ነው።

ማንኛውም ሙያ በውስጡ ድርና ማግ ሆኖ የተሰራ፣ የማይታና የማይዳሰስ መልካም ሥነ-ምግባር አለው። አዎ ሁሉም ሙያ የተገነባው ለበጎ ስራ ነው ማለት ይቻላል።  የሃይማኖትና የባህል ሙያዎችን ለማሳደግ ስንት ሊቃውንት ቀሳውስት ወይም ሽሆች እንደዚሁም ሌሎች ብቁ ሰዎች ይህችን አለም ጥለው እየመነኑ በሺህዎች ለሚቆጠሩ ዘመናት ለፍተውበታል።  እንደ መምህርነት፣ ግብርና፣ ኪነ-ጥበብ፣ ህክምና፣ ህግ፣ ምህንድስና፤ ምጣኔ-ሐብት፣ ጋዜጠኛነት፣ አስተዳደር፣ ወዘተርፈ ያሉ ዘመናዊ ሙያዎችም ቢሆኑ ስንቶች እኛ የምንንሸራሸርበትን መጠጥ ቤት ወይም የምንወላገድበትን ዳንስ ቤት ችላ ብለው ቤተ-ሙከራና ቤተ-መጻሕፍትን ዋሻቸው አድርገው የፈጠሯቸውና ያሳደጓቸው ሙያዎች ናቸው። በሌላ አነጋገር እነዚህ ሙያዎች የተፈጠሩት ህልቆ-መሳፍርት የሌላቸው ጥበቦች፣ መልካም ምግባሮችና በጎ አድራጎቶች አንድ ላይ ተላቁጠውና ተዋህደው ነው። ታዲያ እኛም በዚህ ሙያዎች ውስጥ ገብተን ተምረን ስንወጣ ስጋችንንም ሆነ መንፈሳችን ከሙያችን ጋር አዋህደን ሕብረተሰብን ማገልገል ይጠበቅብን ነበር። ነገር ግን ከጢቂቶች በስተቀር ብዙዎቻችን እንኳን ሙያችንን ልንዋሃደው ከላይ ለብሰነውም አንወጣ። ሙያን ከተከሻችን ላይ ጣል አድርገን የምንወጣውም ወዲያውኑ ከጫንቃችን አውርደን ወደ ሳህንነት እንቀይርና የፍትፍት መዛቂያ ብቻ አድርገነው ቁጭ እንላለን።

በአውሮጳ ቴክኖሎጅ እየመጠቀ በሄደበት በ17ኛውና በ18ኛው ክፍለ-ዘመን ዛሬ በአገራችን እንደምናየው  የመንፈስ ልእልና (moral value) ጉርንቦውን ታንቆ ነበር። በዚያን ዘመን እንዲያውም አንዳድ ጸሐፊዎች *“ የተማሩ ሰዎች በምድር ላይ መታየት ከጀመሩ ወዲህ የሚታመን ሰው ጠፋ”* እያሉ ይጽፉ ነበር። [4] ይህንን አባባል እንዳለ ለመቀበል ቢያስቸግርም አባባሉ ትክክል አይደለም ብሎ ለማጣጣልም የሚያዳግት ይመስለኛል። እንዲያውም ዘገየት ብሎ ህብረተሰቡንም ሆነ የሙያ ቃለ-መሐላቸውን ብቻ ሳይሆን የሰውነት ባህሪያቸውንም የካዱ ምሁራን ሂትለርን፣ ስታሊንና ሞሶሎኒን አገልግለዋል። በአሜሪካን አገር የተወሰኑ ሐኪሞች ሆነ ብለው ጥቁሮችን መድህኒት በመንፈግ የቂጥኝ በሽታ ማጥኛ እቃዎች ወይም እንሰሶች አድርገው ተጠቅመውባቸዋል። [3] ታዲያ ይህንን ያደረጉት ሁሉ ዛሬ የሉም፤ አልፈዋል። ግፉና መጥፎ ስማቸው ግን ለዘላለም ሲነሳ ይኖራል።

አለም ከተፈጠረች ጀምሮ ያለው ጊዜ ከተሰላ ጠቢያም ጥበብ ከተጀመረባቸው አገሮች ትመደባለች ብዬ አምናለሁ። ዳሩ ግን ዘመን እንደ ሰጋር በቅሎ በገሰገሰ ቁጥር በጠቢያ ምድር ጥበብ እንደ ኤሊ መዳህ ያዘ። አእምሮ ተቆለፈ፤ አይን እንዳያይ ታፈነ፤ ጆርምም እንዳያይ ተወተፈ። አንደበት እንዳይናገር ሲዘጋ፣ ጣትም እንዳይጽፍ ተቀየደ። በዚህና በሌሎችም ምክንያቶች ዛሬም በሬ ጠምደን ጭንጫ መሬት እናርሳለን፤ አውራ ጣታችንን በቀለም እየቀባን እንፈርማለን።  ቢሆንም እኛ ፈልገን ባናመጣውም በአለም ላይ ሌት ተቀን እንደ ዶፍ የሚወረደው የእውቀትና የጥበብ ዝናብ አውሮጳንና አሜሪካ ሲጠበው ወደኛም የተቆለፈውን በር በርግዶ መፍሰስ ቃጣው። የተማሩ ሰዎች ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ። ታዲያ እንደዚያ በ18ኛው ክፍለ ዘመን እንደነበረችዋ አውሮጳ ተማርን የምንል ሰዎች በበዛን ቁጥር የመንፈስ ልእልናና የሙያ ሥነ-ምግባር እየኮሰመነ መጣ።  ሰርቲፊኬት፣ ዲፕሎማ፣ ዲግሪ፣ ቆብና መስቀል እንደ አናጢ መርቴሎ የእንጀራ መበያ ብቻ ሆነ። ተማርን የምንል አፈ ጮሌዎችና ህሊና ቢሶች አለም አንድ እየሆነች በመጣችበት ዘመን ሰው መርጦ ባልተወለደበት የዘር ግንድና ቋንቋ የወጣንበትን ሕብረተሰብ እየከፋሉ ለሚያናክሱት አገልጋዮች ሆንና አረፍነው። የፈጠራ ታሪክ እያወራን አንዱን ጎሳ ከሌላው፣ ይህኛውን መንደር ከዚያኛው ስናጋጭ የምንውል ፊደል ቆጥረናል የምንል ሰዎች ነን። ዝርዝሩ ብዙ ነው። ደግነቱ ሂትለርን ሲያገለግሉት እንደነበሩት ምሁራን ሁሉ እኛም እናልፋለን። አዎ አናመልጥም። በተዘዋዋሪም ሆነ በቀጥታ መንገድ የምንፈጽመው ግፍ ግን እስከ አለም ፍጻሜም አያልፍም።

ኢማኑኤል ካንት (Emanuel Kant) በትክክል እንዳስቀመጠው ትምህርት ብቻውን ሰውን ጥሩ አያደርገውም። [4] እንዲያውም ለማጭበርበር የሰላ ጮሌ አድርጎ ሊያዘጋጀው ይችላል። ዛሬም ቢሆን በአውሮጳም ሆነ በአሜሪካ ትምህርት የሰላ አጭበርባሪ አድርጎ ያዘጋጃቸው በርካታ ሰዎች አሉ። ነገር ግን እንዲህ አይነት ፊደል ቆጣሪዎች በእነዚህ አገሮች በሕብረተሰቡ ዘንድ ጥፋት እንዳያደርሱ “ የመናገር ነጻነት” የሚባል ቅዱስ መንፈስ ተብትቦ ይዟቸዋል። ጸሐፊ፣ ጋዜጠኛ፣ ፎቶ-አንሺ ወዘተ እየተከተለ ጉዳቸውን ሁሉ እያዋጣ ቀደም ብሎ ለሕዝብ ያጋልጣቸዋል። በጠቢያ ምድር ግን የመናገር ነጻነት  በልጓም ተሸብቦ ተይዟል። ይህም በመሆኑ “ፊደል ቆጣሪ” በታወቀ ሥርዓተ-ትምህርት አልፎም ሆነ በግኘ መልክ ያገኘውን ዲፕሎማ እያሳየ ከዲፕሎማው ጋር የሚመጣውን የሥነ-ምግባር ግዴታ ፍቆና ልጦ እያስወገደ ሕዝብ የደም እንባ ለሚያስለቅሱ ከንቱዎች “በሚኒስቴርነት”፣ “በዩኒቨርሲቲ አስተዳዳሪነት”፣ “በአምባሳደርነት” አንዳንዴ እንዲያውም በነፍሰ-ገዳይነትም ተቀጥሮ ሲያገለግል ይውላል።

ይህ ዘመን ለጦቢያ አደገኛ ዘመን ነው። መነኩሴው ሳጠለቀው ቆብ፣ ቄሱም ለጨበጠው መስቀል፣ ሰባኪው ለተሸከመው ምጽሐፍ ቅዱስ፣ ሼኩም ለቁርዓኑ፣ ሌላውም ባለሙያ ለተካነበት ሙያ መገዛቱን ትቷል። እንዲያውም እነዚህን ለሰው መዳኛ እንዲሆኑ የተፈጠሩትን እሴቶች ሕዝብን ለማሰቃየት ሲጠቀምባቸው ይውላል። በሂትለር ዘመን ቢያንስ 23 ሐኪሞች በጦርና በኢሰበአዊ ድርጊት ወንጀል ላይ ተሳትፈው ነበር። ከእነዚህ ወንጀሎችም አንዱ በእሰረኞች ላይ ያለ ፈቃዳቸው ምርምር ማድረግ ነበር። በዚህም ምክንያት ብዞዎቹ እሰረኞች ሲሞቱ በርካታዎች ደግሞ አካለ-ጎደሎ ሆነው ነበር። ይህ አሰቃቂ አጋጣሚም ቆይቶ ወንጀል የሰሩትን "ባለሙያዎች" ሕግ ፊት እንዲቀርቡ ከማድረጉም ባሻገር በምርምር ታሪክ ውስጥ ታላቅ ምእራፍ የሆነውን ኑሪምበርግ ኢቲካል ኮድ (Nuremberg code) እንዲፈጠር አድርጓል። ይህ "ኮድ" ባጭሩ ተመራማሪዎች በሰዎች ላይ ምርምር ሲያደርጉ መከተል የሚገባቸውን ግዴታዎች ይዟል። እንደሚታወቀው ደንብ ወይም ሕግ እንዲፈጠር የሚያደርገው ከሥርዓት ዉጪ የሆኑ ሰዎች መከሰት ነው። የሙሴ ሕግም ከሰማይ የወረደው እንደዚህ እንደዛሬው የሰው ልጅ የሚይይዝ የሚጨብጠውን አጥቶ አንዱ ሌላውን የሚበላበት ጊዜ በመከሰቱ ይመስለኛል።

ስለዚህ እኛ ጦቢያውያን ፊደል ቆጣሪዎች ህሊናችን፣ ባህላችን፣ ሃይማኖታችንም ሆነ ሙያችን ሊገዛን ስላልቻለ የወጣንበት ህብረተሰብ ከጥፋት ለማዳን ደንብና ስርዓት ያስፈልገናል። አዎ አሁን እንደሚታየው ኢትዮጵያን ጠብቀዋት የኖሩት የሽምግልና ተቋማት ክፉኛ ተደርምሰዋል። የሃይማቶት ተቋማት አስተዳደሮችም ነቀዝ በልቷቸዋል። በሙያ የመገዛት ባህሪም መቀመቅ በመውረድ ላይ ይገኛል። ምንም እንኳ ደንብና ህግ በህሊና እስኳል ላይ የተገነቡትን ሽምግልናን፣ ክህነትን፣ ባህልና ሙያን ባይተኩም ጦቢያውያንን ከ"ባለሙያ" ወንጀለኞች ለመከላከል የሚከተሉት መንግስታዊ ያልሆኑ (non-governmental) ተቋማት ቢቋቋሙ የሚበጅ ይመስለኛል።

፩. ሃይማኖታዊ ሥርዓት-ትምህርትን ጨምሮ የትምህርት መርሀ-ግብርን (curriculum) የሚፈትሽ አካል

፪. የትምህርት ተቋማት በአካልና በአእምሮ የዳበረ ዜጋ ለማፍራት የተዘጋጁ መሆናቸውን የሚከታተል አካል (Institution credentialing Agency)

፫. በየዘርፉ ከሃይማኖትም ሆነ ከዘመናዊ የትምህርት ተቋማት የሚወጡ ባለሙያዎችን የሙያ ብቃት የሚፍትሽ ፈተና አዘጋጅ ኮሚቴ ((certification and re-certification committee)

፬. ለሰው ልጅ እድገትና ብልጽግና ላቅ ያለ አስተዋጽኦ በሙያቸውም ሆነ በሌላ ዘርፍ ያበረከቱ ዜጎችን በክብር የሚሸልምና በአንጻሩም ሙያቸውን ህብረተሰብን ለሚጎዳ ነገር ያዋሉትን ደግሞ በህይወት እያሉም ሆነ አልፈው ክብራቸውን የሚገፍ አካል

፭. ሂትለርን ሲያገለግሉት እንደነበሩት ሁሉ ከአረመኔዎች ጋር ሆነው ወንጀል የሰሩትን "ባለሙያዎች" በህይወት እያሉም ሆነ ሞተው ለፍርድ የሚያቀርብ አካል

አመሰግናለሁ።


*ዋቢ (All last time accessed on 10/2/09)*

1. *http://www.huffingtonpost.com/hanna-ingber-win/mothers-of-ethiopia-part_b_300333.html*
2. *WHO stastical information sytem http://www.who.int/whosis/en/*
3. *The Tuskegee Syphilis Experiment http://www.infoplease.com/ipa/A0762136.html*
4. *Emanuel Kant: Page 197 The Story of Philosophy, Will Durant, Fifth edition 1933*
5. *History or Research Ethics: http://research.unlv.edu/OPRS/history-ethics.htm (accessed on 10/2/09)*


*መስከረም ሁለት ሺህ ሁለት ዓ. ም.*